# ምክር ቤቱ የህንድ ልዑካን ቡድንን ተቀብሎ አነጋገረ



የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልአኩ እዘዘው (ኢንጂነር) ከምክር ቤቱ ምክትል ዋና ፀሐፊ ውቤ መንግሥቱና ከምክር ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎች ጋር በመሆን መጋቢት 17 ቀን 2010 ዓ.ም. በህንድ ዓለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅ ማሽነሪ ኤግዚቢሽን ማህበር (India International Textile Machinery Exhibitions Society /India ITME Society) ሊቀመንበር ሃሪ ሻንካር የተመራውን የህንድ የቢዝነስ ልዑካን ቡድንን በምክር ቤቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

የልዑካን ቡድኑ የጉብኝት ዓላማ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ያለውን የንግድ ግንኙነት የበለጠ ለማጠናከር ሲሆን በተለይ ደግሞ በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ በጋራ መሥራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለመወያየት ነው፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት በኢትዮጵያ በጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ ያለውን እምቅ አቅም እና የኢትዮጵያ መንግሥት ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪው ዕድገት እየሰጠ ያለውን ትኩረት በማስታወስ ማህበሩ በኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ እና በህንድ የጨርቃ ጨርቅ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ መካከል አጋርነት ለመፍጠር ያሳየውን ፍላጎት በደስታ መቀበላቸውን ገልጸዋል፡፡

የማህበሩ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ወ/ሮ ሄማ ሰሪቫስታቫ በበኩላቸው ማህበሩ የህንድ ኢንቨስትመንትን እና ሌሎች የንግድና የሥራ ዕድሎችን ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ ያላሰለሰ ሥራ እንደሚሠራም እምነታቸውን ገልጸዋል፡፡

የህንድ የጨርቃ ጨርቅ ኤግዚቢሽን ማህበር ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት እ.ኤ.አ. ከ1980 ጀምሮ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ኤግዚቢሽን እንደሚያካሂድ የገለጹት ዋና ዳይሬክተሯ በኢትዮጵያም ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን የማካሄድ ፍላጎት እንዳለው ተናግረዋል፤ በዚህ ረገድ በሁለቱም ሀገሮች የግሉ ዘርፍ መሃል አጋርነት መመሥረትም ይፈልጋሉ፡፡

በመጨረሻም በመጪው ህዳር መጀመሪያ ላይ በሚካሄደው ፲ኛው ኢትዮ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ የህንድ ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ምርቶቻቸውን እንዲያሳዩ ማህበሩ ተጋብዟል፡፡

## ዋና ፀሐፊው የጀርመን ንግድ ምክር ቤት ተወካይን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ



የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ፀሐፊ እንዳልካቸው ስሜ በጀርመን ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት (IHK / Chamber of Commerce and Industry Reutlingen, Germany) ዓለም አቀፍ ንግድ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ማርቲን ፋሃሊንግ ጋር መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም. በጽ/ቤታቸው በምክር ቤቶቹ የትብብር ጉዳዮች ላይ ተወያዩ፡፡

ኃላፊዎቹ የጀርመን ምክር ቤት ለግሉ ዘርፍ ሊያደርግ በሚችለው ዘርፈ ብዙ ድጋፎች ዙሪያ የተወያዩ ሲሆን፣ በተለይ በአቅም ግንባታ፣ በፋይናንስ እና በቴክኒካል ድጋፎች ዙሪያ መሥራት በሚችሉባቸው አግባቦች ላይ ሀሳብ ተለዋውጠዋል፡፡

## ም/ቤቱ የአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነትን አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ



የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የአፍሪካ አህጉር ነፃ የንግድ ቀጠና ስምምነትን አስመልክቶ መጋቢት 17/2010 ዓ.ም. ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጠ፡፡

የምክር ቤቱ ፕሬዚደንት ኢንጂነር መልአኩ እዘዘው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ኢትዮጵያ መጋቢት 12/2010 ዓ.ም. ኪጋሊ ሩዋንዳ "የአፍሪካ አህጉር የነፃ የንግድ ቀጠና" ስምምነትን ከተፈራረሙ 44 አገሮች መካከል አንዷ ስትሆን ምርቶቿን በመላዉ የአፍሪካ አሁጉር ለሚገኙ ተጠቃሚዎች አልማ በማምረትና በመላክ ገበያዋን እንድታሰፋ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ይረዳታል፡፡ ኢንጂነር መልአኩ ጨምረው እንደገለፁት ከስምምነቱ የሚገኘውን እድል በአግባቡ ለመጠቀም እና በአህጉሩ ውስጥ በሚገኙ ገበያዎች ላይ ተወዳዳሪ ለመሆን የግሉ ዘርፍ አቅም ከመቼውም በላይ መጠናከር ያስፈልገዋል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ፀሀፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ በበኩላቸው እንዳሉት ስምምነቱ የአፍሪካ ህብረት በ2063 አጀንዳው ሊሰራ ካቀዳቸው ዋና ዋና ተግባራት አንደኛው መሆኑን ጠቅሰው በተለይም የማኑፋክቸሪንጉ ዘርፍ ምርትን አምርቶ በአህጉሩ ላሉ አገሮች ያለ ኢምፖርት ታሪፍ ለመላክ እድል ይከፍታል።

በመግለጫው ላይ በጋዜጠኞች ለተነሱ ጥያቄዎች የምክር ቤቱ ፕሬዚደንትና ዋና ፀሀፊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

## ECCSA-India ITME Society: Partner-



Melaku Ezezew (Eng.), President of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), along with Wubie Mengistu, Deputy Secretary General of ECCSA, received on 26th of March, 2018 a four member Indian delegation headed by S. Hari Shankar, Chairman of India International Textile Machinery Exhibitions Society (India ITME Society) at the Board Room of ECCSA.

The aim of the delegation's visit is to look for business partnership among the respective businesses of the countries in the textile sector.

Stating the untapped potential that exists in the textile sector and the priority given by Ethiopian government to the development of the industry, Melaku warmly welcomed the interest India ITME Society showed to build synergy between the textile industry of Ethiopia and the textile engineering industry of India.

According to Seema Srivastava, Executive Director of India ITME Society, the Society would work to bring investments, more opportunities and employments to Ethiopia with view of benefiting businesses of both sides.

The India ITME Society has been organizing a textile machinery exhibition since 1980 every four years for the development of modern technology for manufacturing, and has interest to organize international exhibition in Ethiopia and need local partners.

Finally, ECCSA offered an invitation to the India ITME Society to bring Indian companies to exhibit in the 11th Ethio-Chamber International Trade Fair to be held in Early November, 2018 in Addis Ababa.

## ECCSA-IHK: Talk on Strengthening Cooperation



Endalkachew Sime, Secretary General of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA), held on 27th of March, 2018 a short business cooperation conversation with Martin Fahling, Managing Director International Trade in IHK (Chamber of Commerce and Industry Reutlingen, Germany) at his office.

The officials discussed on areas of assistant engagement IHK may provide to ECCSA/BMOs.

The two sides agreed that they should strongly work basically in three core areas of strengthening regional integration, supporting the Public Private Dialogue (PPD), and capacity building, financial resources and technical supports.

## Press Conference on AfCFTAA Held



The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) organized a press conference on 26th March, 2018 regarding the African Continent Free Trade Area Agreement (AfCFTAA), which was signed on 21st March, 2018 at Kigali, Rwanda.

President of ECCSA, Melaku Ezezew (Eng.), in his press briefing, said Ethiopia is one of the forty four countries that signed AfCFTAA, which is expected to bring great opportunities to Ethiopia to attract investment and widen its market throughout the whole African countries in exporting its products. The capacity of the business community of the country should be heightened to be competitive in the markets of the continent, he added.

Ato Endalkachew Sime, Secretary General of ECCSA, on his part said that the agreement is one of the milestones to implement the Agenda 2063 of African Union, which will open opportunity especially to the manufacturing sectors in Ethiopia to export their products to African countries without import tariff.

On the press conference, questions raised by the journalists regarding the African Continent Free Trade Area Agreement have been responded by the President and the Secretary General of ECCSA.